በ_ብ

የኔ ቤት ሁል ጊዜ ባለሁበት ነው
የኔ ቤት ጭንቅላቴ ውስጥ ነው
የኔ ቤት የማስበው ወይ እንዳሰብኩት በማስበው ነገር ላይ
ጭንቅላቴን የማሳርፍበት ቦታ'' ያ ነው የኔ ቤት
የኔ ቤት የሆነ ቦታ እንዳለው በቁስ የተሰራ አይደለም
የኔ ቤት ጭንቅላቴ ውስጥ ነው''

ቤት



# Gary Anderson Interviews Bob Marley

**ጥ፡** እንዴት ናችሁ በድጋሜ Gary Anderson እባላለሁ ከCCTV ዛሬ ከኔ ጋር ቦብ ማርሊ እና ዌለርስ’ ቦብ ማርሊ ከመጀመሪያዎቹ ዌለርስ ከ ፒተር ታሽ እና በኒ ጋር አባልም ነው እና ዛሬ ቦብ Georgia State ነው አዲሱ አልበሙን ለማስተዋወቅ እንዲሁም ነገ ምሽትም Atlanta  ይገኛል’

የት ነው የምትጫወተው ቦብ?

**መ፡** አሪፍ ትያትር ያሉት አለ እዛ ነው የምጫወተው

**ጥ፡** The Fox ነው?

**መ፡** አዎ The Fox  The Fox

**ጥ፡** ባለፈው world Tour ጊዜ  New Orleans and Miami መጥተህ አትላንታን አልፈህ ሄደህ ነበር’

**መ፡** እንደእሱ እንኳን ሳይሆን’ አንዳንዴ’ አንዳንዴ ታቃለህ’ አንዳንዴ አርቲስቱ አይደለም’ አንዳንዴ ሰበቡ ሁሉ አርቲስቱ ላይ ይመጣል’ አርቲስቱ ግን ሳይሆን ማለት ነው ታቃለህ’ አንዳንዴ ከተማው’ አንዳንዴ ፕሮሞተር’ አንዳንዴ የአመራር ወይ የአለመግባባት ችግር ይሆናል ታቃለህ’

**መ፡** ሁልጊዜ ችግሩ የአርቲስቱ ይሆናል ብዬ ግን አላስብም ምክንያቱም አርቲስቱ ሁልጊዜ ለህዝቡ ነው እና ችግር ሲመጣ ሁልጊዜ የአርቲስቱ አይደለም ሁልጊዜ የበለጠውን ነገር የሚጫወቱት ሰዎች እንጂ

**ጥ፡** እዚህ ግን ተቀጥረህ ነበር ባለፈው

**መ፡** አዎ ባለፈው እዚህ በምመጣበት ጊዜ ጉዳት አጋጠመኝ እና እዚህ መድረስ አልቻልኩም’ ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነው

**ጥ፡** ቦብ ትንሽ ስለሃይማኖትህ ለመጠየቅ ፈለኩ
አንተ ራስታፋራይ ነህ አይደል?
ራስተፈሪ የናንተ ታላቁ ነብይ እንደሆነ ነው ምታምነው?

**መ፡** አዎ እሱ የኛ አምላክ ነው

**ጥ፡** እና ራስታፋራይን አሜሪካ ውስጥ ለማስተዋወቅ እየሞከርክ ነው ወይስ?

**መ፡** ራስታፋራይ ትክክለኛ ባለሙሉ መብት የምድር ገዢ ነው ታቃለህ’ የምር እየሞከርን እንኳን አይደለም ምክንያቱም ራስታን መቀየር አትችልም እኔ ነኝ የሆንኩት’ መሆን አለብህ ስትፈጠር’

ስለዚህ እኛ እየተስማማን ያለነው መጥተን የህዝቡን ህሊና አንድ ለማድረግ ነው

ብዙ ሰዎች አምላክ በህይወት እዚህ እንዳለና የሱም ስም ራስተፈሪ እንደሆነ አያውቁም

**መ፡** አንዳንድ ሰዎች አምላክ እንደ ክርስቶስ ሆኖ ተመልሶ እንደሚመጣ ነው አሁንም የሚያውቁት ግን ተመልሶ ሲመጣ አዲስ ስምም እንደሚኖረው ይነግርሃል ስለዚህ ተመልሶ ሲመጣ እየሱስ ክርስቶስን ድጋሚ አይሆንም' ያም ማለት ዛሬ በአዲስ ስም ሲመጣ ራስተፈሪ' ሆኖ ነው ስለዚህ የራስታ ሐዋርያት ማለት የክርስቶስ ሐዋርያት እንደማለት ነው' ገብቶኃል አባባሌ'

**ጥ፡** ራስተፈሪያን ጃማይካ ውስጥ ያሉትን ጥቁር ህዝቦችን የሚመለከቱት ባቢላን ውስጥ እንዳሉ ስደተኞች ነገር ነው?

**መ፡** ምንመለከተው አ' እሺ ያ ማን
ታሪክ ታሪክ እንደዛ እንኳን አይደለም የምናየው እራሳችንን ግን የሆነው ነገር እንደዛ ነው' ምክንያት ታሪክ በባሪያ ንግድ አማካኝነት ከአፍሪካ ወደ ምዕራብ አሜሪካ ወደ ሁሉም ቦታ ገብቶኃል 'ያ ተፈጥሮ ነው አሁን እዚህ ነው ያለነው አይደለም' ከአፍሪካ እንደ ባሪያ ሆነን ነው' የተሰረቅነው አፍሪካዊ ነን

አሁን ጃማይካ መጥተህ ጃማይካ ወስደውህ እና ዛሬ ጃማይካዊ መሆን አለብህ ወይ አሜሪካዊ መሆን አለብህ? አይሆንም' አንፈልግም' እንደዛ እንድንጠራ እኛ አፍሪካዊ ነን ታቃለህ'

አሁን የሆነ ሰው ጥቁር ህዝብ ለብቻቸው ህንዳዊያን ለብቻቸው ቻይናዊያን ለብቻቸው ቢል አይደለም ለዛ ነው ክርስቶስ በአዲስ ስም እመለሳለሁ ያለው አዲሱ ስምም ራስተፈሪ' ነው ለሁሉም ህዝብ ታቃለህ ለዛ ነው ምስማማው አምላክ ፈጣሪ ነው በሚለው ታቃለህ' በቀላሉ

**ጥ፡** ስለዚህ አለም ላይ ያሉ ጥቁር ህዝቦች አንድ ከሆኑ በኋላ ወደ አፍሪካ እንዲመለሱ ነው የምትፈልገው?

**መ፡** አንዴ አንድ ከሆንክ' አንዴ አንድ ከሆንክ አንድ የምትሆነው በአፍሪካ ምክንያት ነው ከዛ የክርስቶስ መንግስት ምድርን መምራት አለበት

አሁን ወደ አፍሪካ መመለስ የፈለገ መመለስ አለበት አሁን ያለህበት' አሁን ምትኖርበት ቦታ የሚጎዳህ ከሆነ' ያ ያንተ የግል ውሳኔ ነው' ነገሩ ግን የክርስቶስ መንግስት ምድርን መምራት አለበት' ክርስቶስ ደግሞ ራስተፈሪ ነው ታቃለህ'



**ጥ፡** ያንተ ማስታወሻ አዲሱ አልበምህ ላይ
ስለ ባቢሎን ሲስተም ታወራለህ?

**መ፡** አዎ

**ጥ፡** ባቢሎን ሲስተም ላይ ምንድነው ያየህው?

**መ፡** ባቢሎን ሲስተም ቫንፓየር ነው'
ህዝቡን ቀን በቀን እያታለለ ትምህርት ቤት'
ቤተ ክርስትያን እየገነባ'

ምክንያት' ቤተ ክርስትያኑን ስናረጋግጥ አሁን' መፅሐፍ ቅዱሱ እዛው ነው ያለው' መፅሐፍ ቅዱሱ ሲገለጥ ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ ንጉሰ ነገስት የጌቶች ጌታ ይሆናል' ይላል አይደል አሁን ስንመለከት ኃይለስላሴን አየን'

ትምህርት ቤቱን ስንመለከት ደግሞ አሁን
ትምህርት ቤቱ ስለተፈጥሮአዊ ታሪክ ወይንም ስለሰው ልጅ መጀመሪያ አመጣጥ ለህዝቡ አያስተምርም' የበለጠ የሚነግሩህ ስለአሜሪካ ታሪክ ስለጃማይካ ታሪክ ነው
ስለህዝቡ ታሪክስ? ከመጀመሪያው ?

ለመናገር የሚሞክሩት ህዝቡ የመጣው ከዝንጀሮ ነው ብለው ነው' ዝንጀሮ ከመቼ ጀምሮ ነው መቀየር ያቆመው' ታቃለህ'
ለዛ ነው ህዝቡ የእግዛብሔር ፍጥረት ናቸው
በሚለው የምስማማው

**መ፡** እና እኔ እንዳገኘሁት ከሆነ ሰዎች ቀላል ናቸው' ምክንያቱም ታስተምራቸው እና ትልካቸውና ገብቶኋል'
የሆነ የተማሩ ይሆናሉ' በጣም በጣም ሸዋጅ ነገር ነው

ራስህን ነው መሆን ያለብህ ታቃለህ'

**ጥ፡** ይሄንን መልዕክት ነው አሜሪካ ውስጥ ላሉ ጥቁር ህዝቦች ማስተላለፍ የምትፈልገው?

**መ፡** ይሄ መልዕክት 'ይሄ መልዕክት 'ይሄ መልዕክት' ነው ህዝቡ ያለው' ይሄ ዛሬ ላይ ያሉ ህዝቦች መልዕክት ነው ታቃለህ' ይሄ ትውልድ ነው አምላክን ያየው' ለዛ ነው ዛሬ ላይ ስንመጣ የቀለም አድልዎ የሌለን ምክንያት ታቃለህ' ከዚህ ጋር አንስማማም የምንስማማው ይሄ ትውልድ ነው አምላክ እነዚህን ህዝብ ያየው ታቃለህ' ይሄ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው ሁሉም የህዝብ ነገር ነው ይሄ ትውልድ ነው አምላክን ያየው

ግን ስትረዳው ጥቁር ሰው የጥበብ' የእውቀት እና የመረዳት ስጦታ ተሰጥቶታል'' ነጭ ሰው የቴክኖሎጂ ስጦታ ተሰጥቶታል'' እስያዊ የሆነው ሰው ደሞ የሃብት ስጦታ ተሰጥቶታል'' የመልከአምድሮች ምናምን አይነት አይደል

ስለዚህ ጥቁሩ ህዝብ አንድ ካልሆነ ያም ማለት ነጩ ህዝብ ጥቅም የለውም' ምክንያቱም አንድነት የለውም አቅጣጫ ለመስጠት ለዛ ነው የተፈጠሩት ነገሮች የሚወዳድቁት ምክንያቱም ስሩ ያንን እውቀት ያገኘበት አንድ አልሆነም ያም ማለት የምድር መንግስት የክርስቶስ መንግስት ሰው የሰራቸው ነገር ላይ ተፈጥሮዊ አንድነት ሊኖረው ይገባል

**መ፡** ምክንያት የሆነ ሰው ጨረቃ ላይ ለመሄድ አንድ ሁለት የህዋ መርከብ ለመስራት ሳይንቲስቶችን ሲያበረታታ ታቃለህ'

የክርስቶስ መንግስት ላይ ግን የሚነገርህ አንድ ሁለት ቤት እንድትሰራ ተጨማሪ ምግብ እንድትተክል' የምድሩን ህዝብ ሚኖርበትን ማመቻቸት ነው' ከዛ በፊት ገብቶኋል አባባሌ'' ከዛ በፊት በበቂ ህዝቡን ትክክል ማድረግ ነው ጥሩ የሚያስብለው ታቃለህ ' የክርስቶስ መንግስት ሚኖረው ለዛ ነው

ምክንያት ሁሉም ሰው ውስጥ እውነት' የሚባል ስም ነገር አለ ታቃለህ' እውነት ባይኖር ሳናግርህ እኝ አትለኝም ሰዎች ሰው ባይሆኑ ሳዋራህ እውነት ስትሰማ አዎ አትለኝም'' ጭንቅላትህን አገናዝበህ አይ ይሄ ውሸት ነው አትልም' ምክንያት ያንነው ሲስተሙ የሚያስተምረው '

ሰዎች ተፈጥሮዊ የሆኑ ሰዎች እውነት ሲሰሙ ያቋርጣሉ ምክንያት ሲስተሙ ራሱ የሚያስተምረው' አይ እውነቱን መናገር የለብህም' ቀጥታ በቃ ሮቦት ነው መሆን ያለብህ ይልሃል'

የተጠየከውን ትመልሳለህ ማውራት የለብህም ከዛ ወደስራ ትሄዳለህ ታቃለህ' ለዛ ነው ዛሬ የባቢሎን ሲስተም ቫንፓየር የሆነው'' ቫንፓየርነት ነው ታቃለህ' ለኔ

**ጥ፡** እንዴት ነው ህዝቡ ይሄን ነገር መከላከል ያለበት?

**መ፡** ጊዜው ደርሷል ማን' ጊዜው ደርሷል
ብዙኃኑ ህዝብ ይወድቃሉ የተወሰኑትም ይተርፋሉ

**መ፡** ስለዚህ ዛሬ አለም ላይ ሰው የሰራቸውን መሳሪያዎች ስንመለከት አምላክን መዋጋት አይችሉበትም'' ማለት አምላክን በመሳሪያ መዋጋት አትችልም' ስለዚህ ሰው እራሱን ይዋጋበታል''

ስለዚህ
ስትመለከት መጥፎ ሰዎች እርስ በርስ ይጣሉበታል'' አምላክ መጥፎው መጥፎውን ያስወግደው ብሏል'' የሆነ ሰው መጥፎው ነኝ ብሎ ሲያስብ ከሱ የባሰ መጥፎ ያጋጥመዋል አየህ ስለዚህ አሁን የምናወራው ስለጥሩነት ነው ምክንያቱም ታቃለህ'' አሁን እሺ መጥፎነት ጥሩ አይደለም ስለዚህ ጥሩነት እንሞክር ጥሩነት ነው የምንፈልገው'' ያነው ሁሉም ነገር ''

**ጥ፡** ግን እንዴት ነው ህዝቡ መሄድ ያለባቸው የባቢሎን ሲስተምን ለማቆም?

**መ፡** እንደተነጋገርነው ህዝቡ እውነቱን እስካወቀ ድረስ ምክንያቱም ''ሁሉም ጉልበት ይንበረከካል ሁሉም ምላስ ይናዘዛል'' እና እግዛብሔር ቀልድ አይደለም ታቃለህ'

እግዛብሔርን ስለ ግል ቢዝነስ አላዋራውም ምክንያቱም ስለማልችል መቻልም ስለማልፈልግ ማድረግ የምችለው ነገር ይሄን የሱን ጊዜ ማለፍ ነው ምክንያቱም እኔ ስመለከት ሰዎች ውስጥ ጥሩነት አለ ሁሉም ውስጥ እውነት አለ'እውነትን የማታገኘባቸው ብቸኛ ሰዎች ሲስተሙ አስተካክሎ በክሎአቸው ያም ማለት ጭንቅላትህን ማትሸጥ ከሆነ የሚኖርህ ጭንቅላት ልክ እንደ ተላላፊ The six million dollar man'' አይነት ይሆንልኃል ገብቶኃል አባባሌ '' ልክ በቃ ቀጥታ ሮቦት ያም ማለት በደንብ ፕሮግራም ተደርገኃል'' ብቸኛው ፕሮግራም ነፃ መሆን ነፃ መሆን ማለት ከእውነት ነፃ

**ጥ፡** ስለዚህ ከሳይንስ ነገሮች ርቀን እንደገና የሰዎችን ስሜት ማዳመጥ መጀመር አለብን?

**መ፡** እንደዛ ብል' እንደዛ ብል ልዩነት አላመጣም ታቃለህ'' ሳይንቲስቶቹ አሁንም እያጠኑ ነው' ምን እያልኩ እንደሆነ እንኳን አይሰሙም' የሚሆነው ነገር ግን እራስህን ታጠፋለህ'' ያ' ያንን ያስውግደዋል ምክንያቱም ነገሮችን ጥሩ ለማድረግ የማትሰራ ከሆነ መጥፎ ለማድረግ ትሰራለህ '' በመጀመሪያ ጉድጓድ ስትቆፍር ሁለት ቆፍር አንድ ለሌላኛው ሰው አንድ ላንተ '' ስለዚህ የሆነ ሰው ሰዎችን ለማስወገድ መሳሪያ ሰራሁ ሲል' እራሱም ሊወገድበት ይችላል ታቃለህ''

እና ችግረኛ ብቻ አይደለም ሁልጊዜ የሚረሳው ትክክለኞቹ የሚጠብቁት ነገር አይጠፋም ገብቶኋል አባባሌ' ስለዚህ ያም ማለት የኛ እጣፋንታ' ' ' ዛሬ ዘመናዊ በሚባለው ጊዜ ሰው የሚነግርህ ነገር እረ ታቃለህ'' ከባድ ነው

# LIGHT

Vol-2

ጥ፡ ጥያቄ
መ፡ መልስ (ቦብ)



**ጥ፡** ሬጌ ሙዚቃ ስሜቱ የሚመስለው' የሚናገረው ብስጭቱ ስለተጨቆኑት የጃማይካ ህዝብ የኑሮ ልምድ ነው' በተመሳሳይ ሁኔታ ሬጌ በጣም ቀላል ቀላል የሆነ ቢት' አብዛኛው የዘፈኖቹ ግጥም ችግራችሁን እርሱ' ደስተኛ ሁኑ' ኑሩ ' እንዴት ነው የምትችለው?

**መ፡** ችግርህን ረስተህ የምትደንሰው?

**ጥ፡** አዎ እንዴት ነው የምትችለው?

**መ፡** ምክንያቱም የምትደንሰው በጃ ሙዚቃ ነው ሁሉም ነገር ያለው ጭንቅላትህ ውስጥ ነው ችግርህን ረስተህ ደንስ ማን ደንስ በጃ ሙዚቃ ባህልህን አውጣ ከባህል በኋላ ወደ እድገት እንሄዳለን''

**ሙ፡** ያንን ነው ማድረግ ያለብህ’ ደንስ በጃ ሙዚቃ ያ ማለት በጃ ሙዚቃ ደንስ ሳይሆን ራስህን በባህል አስተምር ወደ ግርማዊ ራስታ ገብቶኋል አባባሌ’’ ዳንስ ብቻ አይደለም ጭንቅላትህን አስደንስ በጃ ሙዚቃ’ ተራመድ የጃን መንገድ’ አውራ የጃን ንግግር’ ሩጥ የጃን ሩጫ ታቃለህ ’’ ነገሮችህን በጃ መንገድ ስራ እሱም ትክክለኛ መንገድ’ ልክ ትክክለኛ ዳንስ ደንስ ገብቶኋል አባባሌ’’

**ጥ፡** እሺ ይሄ ከባድ ነው ለኔ ለመናገር
ችግሮቹ ጃማይካ ችግሮቹ አሜሪካ ችግሮቹ በሲስተሙ በአለም ዙሪያ ላሉት የተጨቆኑት ህዝቦች በእንደዚህ አይነት የባህል መንገዶች መፍታት እንደሚቻል ይታይኃል? አሪፉ መንገድ ነው ብለህ ታስባለህ ባንተ አስተያየት ስዎችን ለመቅረብ?

**ሙ፡** እኔ ስዎች ላይ ለመቅረብ እየሞከርኩ አይደለም
እኔ እኔ ነኝ አየህ እና በጣም ብዙ የኔ አይነት ስዎች ደግሞ አሉ እዛ ውጭ’ የኔ ህዝቦች

ስለዚህ እንግዳ የሆነ ሰው ለመቅረብ
አልሞክርም’ እኔ የምቀርበው የኔን ህዝቦች ነው ሁላችንም ተመሳሳይ ነገር ነው የምናቀው ሁላችንም ሁላችንም በዚህ ጊዜ የመጣነው የኛ ህዝቦች ነን ማንም አይደለም የኛ ህዝብ ነው ታቃለህ’’ ስለዚህ እንግዳ የሆነ ሰው ላይ ለመውጣት ስትል ግን እንግዳ አይደለም’ ምናልባት ከቆይታ በኋላ አውቀዋለሁ ልትል ትችላለህ ግን የኛ ሰው ነው’

ይቅናህ ጉዞህ ላይ ቦብ አቃለሁ በጣም የተወጣጠረ ጊዜ እንዳለህ
መፍጠን እንዳለብህ
The Fox ትደሰትበታለህ ብያለሁ
The Fox አዎ

እሺ
በድጋሚ አመሰግናለሁ
እንግዲህ ከቦብ እና ዌለርስ ጋር ያደረግነውን ጨውውት ነበረ
እንደተደሰታችሁበት ተስፋ አደርጋለሁ
ወታችሁ ማየትም ትችላላችሁ
ከCCTV Gary Anderson እባላለሁ

እውነት



## Rights

You are permitted to use the resources for any number of personal projects, If you wish to promote this resource on your site, you have the rights to redistribute, however any credit will be much appreciated.

## Prohibitions

You do not have the rights to modify or intended for sale this material

**Yoseph Birhanu**

yosephb764@gmail.com

Addis Ababa 2012 E.C

LIGHT